# የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ላሉባቸው ግለሰቦች የተዘጋጀ የፍትሀዊ መኖሪያ ቤት መመሪያ




www.hud.gov/fairhousingን ይጎብኙ፣ ወይም ለብሔራዊ የመድልዎ ማጉረምረሚያ የስልክ ቁጥር

1-800-669-9777 ወይም 1-800-877-8339 (የፌዴራል ሪሌይ) ይደውሉ

Amharic

## የመኖሪያ ቤት መድልዎ ምንድነው?

ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት ሕግ፣ የአካልጉዳተኞች አሜሪካውያን ሕግ እና የተሃድሶው አንቀፅ 504 ህግ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክል ያሉባቸውን ግለሰቦች ጨምሮ የመኖሪያ ቤት አድልዎ እንዳይፈፀምባቸው ይከላከላል፡፡ የመኖሪያ ቤት አድልዎ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- በአካል ጉዳተኛነትዎ ምክንያት ለእርስዎ ለማከራየት ፈቃደኛ አለመሆን
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢው በማመልከቻ ሂደት ውስጥ እርስዎ አካል ጉዳተኛ ስለመሆንዎ ወይም ስለ እርስዎ አካል ጉዳት ተፈጥሮ ጥያቄ ሲጠየቅ፣ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ሁሉንም አመልካቾች ለአካል ጉዳተኞች ብቻ የሚሆን መኖሪያ ቤት ብቁ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለመለየት የአካል ጉዳተኛ መሆናቸውን ለሁሉም አመልካቾችን ካልጠየቀ በስተቀር
- በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት ለእርስዎ ወይም አንድ ላይ ለሚኖሩት ሰው ስለ መኖሪያ ቤት መረጃ ለመስጠት ወይም ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን
- ተመጣጣኝ ማረፊያን ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን ወይም ለእርስዎም ሆነ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት አብሮቆት ለሚኖር አንድ ሰው ቤትዎን በእኩል እድል ለመጠቀም ወይም በመኖሪያ ቤትዎ ለመደሰት አስፈላጊ ሊሆንብዎት የሚችሉ ምክንያታዊ ማሻሻያዎችን ያለመፍቀድ
- በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት እርስዎን በተወሰኑ ክፍሎች ወይም በመኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ እንዳይኖሩ መገደብ
- በመኖሪያ ቤት ኪራይ ወቅት በአካል ጉዳተኝነት ምክንያትዎ ከፍ ያለ ኪራይ ወይም የደኅንነት ተቀማጭ ገንዘብን የመሳሰሉ የተለያዩ ውሎችን ወይም ሁኔታዎችን ማስቀመጥ
- እርስዎ በድርጅታዊ አሠራር ውስጥ በመኖርዎ መከኒያት የተለያዩ ሰነዶችን ወይም ሁኔታዎችን በመኖሪያ ቤቱ ላይ ማስቀመጥ፣ ለምሳሌ እንደ ተጨማሪ ሰነዶችን መጠየቅ ወይም ተጨማሪ የማረጋገጫ ማጣሪያ ሂደትን ማድረግ
- በአካል ጉዳት ምክንያት ጠንካራ የማጣሪያ መስፈርቶችን መጣል
- በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት እርስዎን ወይም አብሮት የሚኖር ሰውን ማስወጣት
- በአካል ጉዳተኝነትዎ ምክንያት እርስዎን ወይም አብሮዎት የሚኖር ሰው ላይ ትንኮሳ ማድረግ
- ስለ ህክምና ወይም መድሃኒቶች ጥያቄዎችን መጠየቅ
- አንዳይነት ወይም ተመሳሳይ አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ብቻ በስብስብ በተያዙ የቤቶች ልማት ውስጥ እርስዎን ምደባን እንዲቀበሉ መጠየቅ

## ጥበቃ ሚደረግላቸው የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና እና የእድገት እክል ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?

ጥበቃ ሚደረግላቸው አካል ጉዳቶች እንደ ኦርጋኒክ የአንጎል ሲንድሮም፣ ድብርት፣ ጭንቀት፣ ባይፖላር ዲስኦርደር፣ ድህረ-አሰቃቂ ክስተት የጭንቀት በሽታ (PTSD)፣ የተወሰኑ የመማር እክሎች፣ ኦቲዝም፣ ዝቅተኛ የአእምሮ ጤንነትን፣ የአሰቃቂ ክስተት አእምሮዋዊ ጉዳቶች፣ የአልኮል ሱሰኝነት እና የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት (በአሁኑ ወቅት ሕገ-ወጥ ዕፅ አጠቃቀም ምክንያት ከሚመጣ ሱስ በስተቀር) የሆኑ የአእምሮ ጤንነት፣ የሳይኮሎጂ፣ የንቃተ ህሊና እናም የእድገት ሁኔታዎች ያለባቸውን ጨምሮ፣ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ያጠቃልላሉ።

## ምክንያታዊ ማረፊያዎች እና ማሻሻያዎች ምንድናቸው?

ተመጣጣኝ ምክንያታዊ ጥቅሞች እና ማሻሻያዎች ለአካል ጉዳተኛዎች መኖሪያ ቤትን የመጠቀም እና የመደሰት እኩል እድል ለመስጠት በሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች፣ አገልግሎቶች ወይም የመኖሪያ ቤት ላይ ሚደረጉ ማሻሻያዎች እና ለውጦች ናቸው። በHUD በሚታገዙ ቤቶች ውስጥ፣ የመኖሪያ ክፍሎች፣ የህዝብ እና የጋራ መጠቀሚያ ቦታዎች ላይ መዋቅራዊ ለውጦች የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ሊያቀርቧቸው ከሚገቡ ምክንያታዊ ማሻሻያዎች ስር ይመደባሉ። አንዳንድ ምክንያታዊ የማሻሻያ ወይም የተሻለ ልወጣ ጥያቄዎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡

- "የቤት እንስሳት ያለመፍቀድ" ፖሊሲ በሚኖርበት ጊዜ ረዳት እንስሳ እንዲኖር መጠየቅ
- ማመልከቻ ወይም ሌላ የወረቀት ሥራን ለመሙላት እርዳታ መጠየቅ
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ረዳት ወይም ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲፈቅድ መጠየቅ
- የመኖሪያ ቤት አቅራቢው የተወሰነ የማመልከቻ ጊዜን እንዲያራዝም ወይም አመቺ የማመልከቻ አሠራሮችን እንዲፈቅድ መጠየቅ
- የማኅበራዊ ዋስትና የአካል ጉዳት ቼክ ወይም የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የአካል ጉዳት ክፍያ እስኪቀበሉ ኪራይ የሚከፈልበትን ቀን እንዲለወጥ መጠየቅ
- ከእንቅስቃሴ ወይም ከሴንሰር ፍላጎትዎ ጋር በተዛመደ መኖሪያ ወይም የጋራ አካባቢ ላይ ተጨባጭ ለውጦችን መጠየቅ
- ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተዛመደ ምክንያት በጊዜ ለጥያቄዎች መልስ ካልሰጡ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ እንዲቆዩ መጠየቅ
- እርስዎ በተጠባባቂዎች ዝርዝር አናት ላይ ሲደርሱ ነገር ግን እንደ ህክምና ወይም ሆስፒታል በመሳሰሉ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር በተዛመደ ምክንያት መንቀሳቀስ ባለመቻል ወደ አንድ ክፍል ለመግባት ተጨማሪ ጊዜን መጠየቅ
- እርስዎ በሆስፒታል ምክንያት ውስን ወይም ጨራሹንም የኪራይ ወይም የሥራ ስምሪት ታሪክ በማይኖረዎት ጊዜ እንደ ማህበራዊ ሰራተኛ ያሉ አማራጭ ዋቢዎችን ማቅረብ

ለተጠየቀው መኖሪያ ወይም ማሻሻያ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የተዛመደ ፍላጎት ሊኖርዎት ይገባል፡፡ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ተጨማሪ ውስን መረጃ ሊጠይቅ የሚችለው የአካል ጉዳትዎ ወይም የመኖሪያ ወይም ማሻሻያ ፍላጎትዎ ለአቅራቢው ግልጥ ያልሆነ ወይም የማይታወቅ ከሆነ ብቻ ነው። የቤት አቅራቢው ጥያቄዎን ከመከልከሉ በፊት ከእርስዎ ጋር መወያየት አለበት.


## አንድ ግለሰብ ማረፊያ ወይም ማሻሻያ መጠየቅ ያለበት መቼ ነው?

ደንብን፣ ፖሊሲን፣ አሠራርን፣ አገልግሎትን ወይም አካላዊ መዋቅርን ለመቀየርና ከመኖሪያ ቤቶችዎ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ለማግኘት ወይም በ HUD በተደገፈ ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ በሚፈልጉበት በማንኛውም ጊዜ። ምን ዓይነት ማረፊያ ወይም ማሻሻያ እየጠየቁ እንዳሉ ማስረዳት አለብዎት። የጥያቄው አስፈላጊነት ለቤቶችዎ አቅራቢ ግልፅ ወይም ቀደም ብሎ የታወቀ ከሆነ ሌላ ማንኛውንም መረጃ ማቅረብ አያስፈልግዎትም። የፍላጎትዎ ጥያቄ ግልፅ ካልሆነ ወይም አቅራቢው የማያውቀው ከሆነ በተጠየቀው መኖሪያ ወይም ማሻሻያ እና በአካል ጉዳተኝነትዎ መካከል ስላለው ግንኙነት ማብራራት ሊኖርብዎት ይችላል። ዝርዝር የሕክምና መረጃ እንዲያቀርቡ አይጠየቁም።

የቤተሰብዎ አባል፣ ጓደኛ ወይም ተሟጋች እንዲሁ ጥያቄውን ሊያቀርቡልዎት ይችላሉ። ጥያቄውን በተወሰነ መንገድ ወይም በተወሰነ ጊዜ እንዲያቀርቡ አይጠየቁም ነገር ግን ጥያቄውን በጽሑፍ ካቀረቡ ብዙውን ጊዜ ጠቃሚ ነው፡፡ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ጥያቄን ለማቅረብ ተመራጭ መንገድ እንዳለው መጠየቅ ይችሉ ይሆናል፡፡ ሆኖም፣ የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች የተመረጡትን ቅጾች ወይም ቅደም ተከተሎች ባይጠቀሙም እንኳ ምክንያታዊ የሆነ የመኖሪያዎን ወይም የማሻሻያ ጥያቄዎን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

# የአእምሮ ጤንነት፣ የንቃተ ህሊና ወይም የእድገት እክሎች ላሉባቸው ግለሰቦች የሚቀርብ ፍትሀዊ መኖሪያ ቤት





**የመኖሪያ ቤት መድልዎ አጋጥሞዎታል? ቅሬታዎን ለHUD ወይም ለአካባቢዎ የፍትሃዊ የመኖሪያ ቤቶች ማእከል ማመልከት ይችላሉ፡፡**

www.hud.gov/fairhousing/fileacomplaint ወይም ለHUD ለብሔራዊ የመድልዎ መስመር በስልክ ቁጥር

**1-800-669-9777** (እንግሊዝኛ/ስፓኒሽ) ወይም **1-800-877-8339** (ፌዴራል ሪሌይ) ይደውሉ

**ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤት አቤቱታ ስላቀረቡ፣ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው በእርሶዎ ላይ እርምጃ ከወሰዱብዎ ይህ ሕጉ-ወጥ ነው፡፡**

እባክዎ የበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን ሊንኮች ይጎብኙ፡የበለጠ ለመረዳት፣ www.hud.gov/fairhousing ን ይጎብኙ ወይም በአካባቢዎ ያለውን የ HUD ቢሮ፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ፍትሃዊ የቤቶች አደረጃጀትን ያነጋግሩ።
እባክዎ የበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን አገናኞች ይጎብኙ፡

- ፍትሃዊ በሆነ የቤቶች ህጎች መሠረት የአካል ጉዳተኞች መብቶች
- ክፍል 504 በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
- በፍትሃዊ የቤቶች ሕግ መሠረት ምክንያታዊ ፍላጎቶች
- በፍትሃዊ የቤቶች ሕግ መሠረት ምክንያታዊ ለውጦች
- በፍትሃዊው የቤቶች ሕግ መሠረት እንስሳን እንደ መክንያታዊ ፍላጎት እንዲወሰድ ያቀረቡትን ጥያቄ መገምገም
- የHUD መግለጫ የቤቶች ሚና የአምስቴድ ግቦችን በማሳካት ላይ